
# አዋልድ መጻሕፍት

አዘጋጅ፡- ዲ/ን ዳንኤል ክብረት



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷአል፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡» 1ኛ ቆሮ. 15፥20-21



«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና፡፡» ሉቃ. 1፥49

## መቅድም

በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ዋሽንግተን ዲሲ አጠገብ በሚገኘው የቅዱስ ማር ቆስ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን በአ ንድ እሑድ ጠዋት ተገኝቼ ነበር። ካህኑ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋዌ ምስጢር ያስተምራሉ። በዚያ ጊዜ ጌታ ችንን በተመለከተ በጽርፈት የተሞላ መጽሐፍ ታትሞ ነበርና፤ በየመሐሉ ያነሡታል። ከትምህርታቸው ሁሉ የማይረሳኝ የሚከተለው ነው፦ «ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲሰድቡ ዝም ስላልናቸው፤ የቅዱሳት መጻሕፍት ራስ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ መሳደብ ጀመሩ። ቅዱሳንን ሲሰ ድቡ ዝም ስላልናቸው የቅዱሳን ራስ የሆነውን ክርስቶስን መሳደብ ጀመሩ። ታድያ እስከ መቼ ዝም እንላለን?»

ይህ ትምህርታቸው አዋልድ መጻሕፍትን በተመለከተ መናፍቃን የስድብ አላቸውን በከፈቱ ቁጥር ትዝ ይለኛል። የሀገሬ ሰውም ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ወይም ቅርጫ ፉን መመልመል ግንዱን ለመቁረጥ ነው ይላል። እንኳን በልጆቹ፣ በአባታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ፤ እንኳን የጸጋ ቅዱሳን በሆኑት ልጆቹ፣ በአባታቸው በባሕሪው ቅዱስ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ፤ ላይ የሚሠነዘረውን ድፍረት የሰማ፣ ያየ፣ ያነበበ ሰው ሁሉ የስድብ አፍ በተሰጠው «በአውሬው» የተቀነባበረ መሆኑን መረዳት ይችላል።

### ለመሆኑ አዋልድ መጻሕፍት እነማን ናቸው?

አዋልድ ቃሉ የግእዝ ሲሆን ትርጉሙም «ልጆች» (በአነስታይ ጾታ) ማለት ሲሆን፤ አዋልድ መጻሕፍት ልጆች የሆኑ መጻሕፍት ማለት ናቸው። ልጅነታቸውም ለመጽሐፍ ቅዱስ ነው። የሚወለዱትም በዘር ሐረግ ሳይሆን በይዘት፣ በመንፈስ፣ በምስጢር፣ በመ ሠረተ ሐሳብ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት «ቀኖናውያት መጻሕፍት» ይባላሉ። ቀኖ ናውያት የሚባሉበትም ምክንያት ቁጥራቸው እና ይዘታቸው ተሰፍሮና ተቆጥሮ የተወሰ ነና የታወቀ ስለሆነ ነው። (ቀኖና የሚለው ቃል መለኪያን ወይም መሥፈሪያን የሚገ ልጽ የግሪክ ቃል ነው።) ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ የተቀነነ (የተወሰኑ) መጻሕፍት ስብ ስብ ነው። እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት «አሥራው መጻሕፍት» ይባላሉ። አሥ ራው ማለት ሥሮች ማለት ሲሆን፤ አሥራው መጻሕፍት ማለትም የሌሎች መጻሕፍት ሥሮች ወይም መገኛዎች (መሠረቶች) ማለት ነው። ስለዚህ አዋልድ መጻሕፍት፤ በአሥራው መጻሕፍት ሥርነት ላይ የሚበቅሉና የሚያድጉ ቅርንጫፎች ናቸው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብና እውነታ ሳይወጡ በእርሱ ላይ ተመሥርተው የመጽሐፍ

ቅዱስን ኃይለ ቃልና ውስጠ ምስጢር ለመተርጎም፣ ለማብራራት፣ ለማተትና ለመተን ተን፣ ለልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉትን በአንድ ላይ ለማሰባሰብ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸው መሠረት ተዛማጅ እና አስረጅ የሆኑ ነገሮችን ለማዘጋጀት፣ ወዘተ የሚጻፉ መጻሕፍት አዋልድ መጻሕፍት ይባላሉ። ይህም ማለት በምስጢርና በይ ዘት፣ በመንፈስና በሐሳብ አስገኚያቸው እና ወላጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህን መሠ ረታዊ ወላጃቸውን (መጽሐፍ ቅዱስን) መስለው የተወለዱና የተገኙ መጻሕፍት ናቸው፤ አዋልድ መጻሕፍት የሚባሉት።

ምንም እንኳ በአንዳንድ ይዘታቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስን ቢመስሉም ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ፣ በጌታችን ከተገለጠውና ከሐዋርያት ጀምሮ ሲያያዝ ከመጣው የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ጋር ተቃርኖ ያላቸው መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች (አዋልድ መጻሕፍት) አይደሉም። እንዲህ ያሉት መጻሕፍት «ዲቃላ መጻሕፍት» ናቸው። ቅድስት ቤተክርስቲያንም ከመሠረታዊ አስተምህሮዋና እምነቷ እና ከቀኖናውያት መጻሕፍት ጋር የማይስማሙትን እንዲህ ያሉትን ማንኛውንም መጻሕፍት ታወግዛቸዋለች እንጂ አትቀበላቸውም።

አዋልድ መጻሕፍትን በተመለከተ በሚከተሉት ነጥቦች መለየት እንደሚቻል ሕንዳዊው የነገረ መለኮት ሊቅ ጢሞቴዎስ አለን ይገልጡታል።

፩. ዓላማቸው መንግሥተ እግዚአብሔር የሆነ፣

፪. በሃሳብ፣ በመንፈስ፣ በምስጢር፣ በነገረ መለኮት ከአሥራው መጻሕፍት እና ከቅዱ ሳት የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ጋር የማይጋጩ፣

፫. ለክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፣ ሞራል፣ ሕይወት እና አነዋወር ተስማሚ የሆኑ፣

፬. በቤተ ክርስቲያን አበው፣ ትውፊት ወይም ጉዞ ምስክር ያላቸው፣

፭. ውስጣዊ ተቃርኖ የሌለባቸው።

እኒሁ ሊቅ የአዋልድ መጻሕፍትን ጉዞ በተመለከተ ሲያትቱ፤ የሰው ዘር እናት እና አባት አዳም እና ሔዋን ናቸው። ልጆቻቸው ግን በዝተው ሞልተዋል፤ ይበዛሉ ይሞላሉም። አዋልድ መጻሕፍትም አባት እናታቸው አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም ልጆቹ ግን በዝ ተዋል ሞልተዋል፤ ይበዛሉም ይሞላሉም። የሰው ዘር እናት እና አባት አዳም እና ሔዋን በየሀገሩ፤ በየዘመኑ ያለ ትወልድ ሁሉ ያውቃቸዋል። ልጆቻቸው ግን በልዩ ልዩ ሀገር በልዩ ልዩ ዘመን ስለተወለዱ ላይተዋወቁ ይችላሉ። አዋልድ መጻሕፍትም በየሀገሩ በየትው ልዱ በተነሡ ቅዱሳን ስለተጻፉ፤ ሰው ሁሉ ላያውቃቸው ይችላል። ከላይ ያሉትን መመ ዘኛዎች እስኪሟሉ ድረስ ግን ሁሉም ይቀበላቸዋል።

አዋልድ መጻሕፍት የምንላቸው ስለ ቅዱሳን ሕይወት የሚገልጹ ገድላት፣ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያስረዱ ትርጓሜያት፣ ሊቃውንት ያስተማሯቸዉን ስብከቶች፣ የጻፏቸው መልእክቶች፣ የጸለዩት ጸሎት፣ የዘመሩት መዝሙር፣ ያዩት ራእይ፣ የጐበኙት ምስጢራዊ ዓለም የተጻፈባቸው ድርሰቶች ናቸው:: እነዚህን በየዘመናቱ ከፍለን እናያቸዋለን::

## ፩. በዘመነ ብሉይ

በዘመነ ብለይ ከአሥራው መጻሕፍት ያልተቆጠሩ ነገር ግን «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርት እና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» /፩ጢሞ.፫÷፲፮/ በተባለው መሠረት ለትምህርት እና ለተግሳጽ ያገለግሉ የነበሩ አዋልድ መጻሕፍት ነበሩ:: ጥቂቶቹን እናንሣቸው::

ሀ. **የያሻር መጽሐፍ:-** «ዳዊት ስለ ሳኦልና ስለ ልጁ ስለ ዮናታን ይህንን የኀዘን ቅኔ ተቀኘ፤ የይሁዳም ልጆች ያስተምሩ ዘንድ አዘዘ፡ እነሆ ይህ በያሻር መጽሐፍ ተጽፎአል።» (፪ሳሙ.፩÷፲፰) ተብሎ የተነገረለትን የያሻር መጽሐፍ የሰብዐ ሊቃናት ትርጉም «መጽሐፈ ልዑላን» ሲለው የሹልጌት ትርጉም ደግሞ «የምርጦች መጽሐፍ» ይለዋል:: ይህ መጽሐፍ መዝሙራት የተሰባሰቡበት መጽሐፍ መሆኑ ይታመናል:: ስለዚህ መጽሐፍ በብሉይ ኪዳን ሁለት ቦታዎች ላይ ተጠቅሶአል:: የመጀመሪያው ኢያሱ አሞራውያ ንን ድል ባደረገ ጊዜ በገባዖን የተፈጸመውን ተአምር በተመለከተ:- «ይህስ በያሻር መጽሐፍ የተጻፈ አይለምን?» ይላል:: ኢያሱ ፲÷፲፫ :: ሁለተኛው ዳግሞ ከፍ ብሎ ያየነው ፪ ሳሙ. ፩÷፲፰ ላይ ያለው ነው::

ለ. **የእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ:-** የሰሎሞንን ታሪክ፣ በእርሱ ዘመን የሆነውን ነገር ሁሉ የሚተርክ መጽሐፍ ፩ነገ. ፲፩÷፵፫::

ሐ. **የእሥራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ:-** የእሥራኤል ነገሥታት የሠሩትን ሥራ እና በዘመናቸው የተፈጸመውን ታሪክ የሚዘረዝር መጽሐፍ ፩ነገ.፲፭÷፴፫፤ ፲፭÷፴፪፤ ፲፮÷፲፬፤ ፲፮÷ ፳፤ ፲፮÷ ፳፯::

መ. **የይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ:-** እሥራኤል ከሁለት ከተከፈለች በኋላ በኢየሩሳሌም ከተማ የነገሡ ነገሥታት ታሪክ የተመዘገበበት መጽሐፍ ፪ነገ.፳÷፳፫፤ ፪÷፳፤ ፲፭÷፮፤

እነዚህ ከላይ የጠቀሰናቸው መጻሕፍት ከአሥራው መጻሕፍት ጋር በቀኖና ባይመዘገቡም፤ ለምክር እና ለትምህርት ይሆኑ ዘንድ ተጠቅሰዋል:: ለምን በቀኖና አልተመዘገቡም? ለሚለው ጥያቄ አብዛኞቹ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት የተስማሙበት መልስ እነዚህ መጻሕፍት፣ ሠፊ ዝርዝር እና በየዘመናቱ የሚመዘገብባቸው በመሆናቸው አልተጠናቀቁም

ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእነርሱ የተገለጸው ታሪክ በአጭሩ በነገሥታት እና በዜና መዋዕል ስለቀረበ ነው የሚል ነው፡፡

ከላይ ከተገለጡት በተጨማሪ የአይሁድ ሊቃውንት በየዘመናቱ ያሰባሰቧቸው የሐተታ፣ የትርጓሜ እና የትምህርት መጻሕፍትም ነበሩ፡፡

ሚሸናህ፡- በዕብራይስጥ ቋንቋ «ዘዳግም» ማለት ነው፡፡ የረበናተ አይሁድን (የአይሁድ መምህራን) ሐሳብ፣ አስተያየት እና ትምህርት የያዘ ሲሆን በቃል ሲወራረስ ቆይቶ በ፪፻ ዓ.ም ረቢ ጃዳድ-ሃ-ናሲ አሰባስበው ጠርዝረውታል፡፡

ገማራ፡- »መደምደሚያ፣ ማጠናቀቂያ» ማለት ነው፡፡ ገማራ የሚሸናህ አንድምታ ሲሆን ሁለት ዓይነት ጥራዝ አለው፡፡ የመጀመሪያው የኢየሩሳሌም ጥራዝ የሚባለውን በ፬ኛው መ/ክ/ዘ ከጌል በፊት የተጠረዘው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የባቢሎናውያን ጥራዝ የሚባለውና በትርጓሜ ስልት ከመጀመሪያው የሚለየው ነው፡፡

ከእነዚህም በተጨማሪ «ዜናሁ ለሙሴ»ን የመሳሰሉ የቅዱሳንን ታሪክ የመዘገቡ መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን ዘመን ነበሩ /ይሁዳ፡ ፲፬/

### ፪. በዘመነ ወንጌል (በሐዲስ ኪዳን ዘመን)

በሐዲስ ኪዳን ዘመን ቅዱሳን ሐዋርያት ከብሉይ ኪዳን እየጠቀሱ የተነገረው ትንቢትና የተሰጠው ተስፋ በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ መሆኑን በማስረዳት ያስተምሩ ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕግ እና በነቢያት የተጻፈውን ለመፈጸም የመጣ መሆኑን ለማስረዳት ሐዋርያት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን መሠረት አድርገው ያስተምሩ ነበር፡፡ /የሐዋ.፩፥፳፮/ ማትያስን ሲሾሙ፤ /የሐዋ.፪፥፲፯/ ለኢየሩሳሌም ተሳላሚዎች ቅዱስ ጴጥሮስ ሲያ ስተምር፤ /የሐዋ.፯/ ቅዱስ እስጢፍኖስ ከአይሁድ ጋር ሲከራከር፤ ሐዋርያት በየመልእክ ቶቻቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ጠቅሰው እየተረጐሙ አስተምረዋል፡፡ (ሮሜ ፫፥፲፤ ፪ቆሮ. ፱፥፱፤ ኤፌ ፬፥፰፤ ዕብራ. ፪፥፭-፲፬፤ ፪ጴጥ. ፩፥፳፩፤ ይሁዳ ፲፬)

ሐዋርያት በቃል ያስተማሩትን በመጽሐፍም መጻፍ ጀመሩ፡፡ በዚህም አራቱ ወንጌሎችና የተለያዩ የሐዋርያት መልእክታት፤ የክርስቶስን ሰው መሆንና የማዳን አገልግሎቱን በመግለጽ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረታዊ (ቀኖናውያት) መጻሕፍት ሆኑ፡፡ ጌታችን ካረገ ከዐሥር ዓመታት በኋላ ወንጌላት እና የሐዋርያት መልእክታት እየተጻፉ በምእመናን እጅ መግባት ጀመሩ፡፡ በዚህም ክርስቲያኖች በቃል የተማሩትን በጽሑፍ ለማግኘት ቻሉ፡፡ ይህም ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው (ቀኖናውያት) የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን አስገኘ፡፡

ሆኖም ቅዱሳን ሐዋርያት በእነዚህ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ አልተወሰኑም። በእነዚህ ላይ የተለያዩ አልዋድ መጻሕፍትን እንዳስፈላጊነታቸው ይጠቀሙ ነበር። በዘመነ ሐዋርያት የብሉይ ኪዳን አዋልድ መጻሕፍት ለማስተማሪያ አገልግሎት ውለው ነበር። ለምሳሌም ሐዋርያው ቅዱስ ጳዉሎስ በ፪ጢሞ. ፫÷፰ «ኢያኔስ እና ኢያንበሬስ» ብሎ የጠራቸው የፈርዖን ጠንቋዮች ስማቸው በሙሴ የአሪት መጻሕፍት በአንዱም አልተጠቀሰም፤ ነገር ግን ከአይሁድ የትውፊት መጻሕፍት በመውሰድ ጠቅሶታል። ወንጌላዊው ማቴዎስም በማቴ.፪÷፳፫ «በነቢያት ናዝራዊ ይባላል» በማለት በዐበይት ነቢያት እና በደቂቅ ነቢያት መጻሕፍት ያልተጠቀሰ ትውፊታዊ ትንቢት መዝግቧል። ሐዋርያው ይሁዳም «ዜናሁ ለሙሴ» ከተሰኘው የሙሴ ገድል ወስዶ ጠቅሷል /ይሁዳ፡ ፱/

በሐዋርያት ዘመንና በራሳቸው በሐዋርያት የተጻፉ መጻሕፍትና መልእክታት የመጽሐፍ ቅዱስ (የቀኖናውያት መጻሕፍት) አካላት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የምንለው ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በሐዲስ ኪዳን ሐዋርያት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከቃሉ የተማሩትንና በዓይናቸው ያዩትን በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጥበቃ ሆነው የጻፏቸውን መጻሕፍት ነው። ከሐዋርያት በኋላ በተነሡ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተጻፉ መጻሕፍት የሚመደቡት ከሐዲስ ኪዳን አዋልድ መጻሕፍት ውስጥ ነው።

እነዚህ በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተጻፉ መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይቆጠሩም፣ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የመጻፍ ሂደት በመጽሐፍ ቅዱስ ያበቃና የተደመደመ አይደለም። ጌታችን ከሐዋርያት ጋር እንደነበረ ሁሉ ከዚያ በኋላ በሐዋርያት ቦታ ከሚተኩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋርም አለና። «እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» እንዳለ። ማቴ. ፳፰÷፳።

መድኃኒታችን በምሳሌ ሲያስተምር ወንበዴዎች ደብድበው በሞትና በሕይወት መካከል ጥለውት ስለሄዱ አንድ መንገደኛ አስተምሮአል። ይህን ቁስለኛ አንድ ርኅሩኅ ሳምራዊ ወደ እንግዳ ማደሪያ ቤት ወስዶ ከጠበቀው በኋላ በማግሥቱ ለእንግዶች ማደሪያ ቤት ጠባቂው ሁለት ዲናር አውጥቶ ሰጠውና «ጠብቀው፣ ከዚህ በላይ የምትከሥረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ» አለው። ሉቃ.፲÷፴፭። ይህ ምሳሌ ነው። በወንበዴዎች የቆሰለው ቁስለኛ አዳም፣ በአጠቃላይ በኃጢአት መርዝ የተለከፈና የቆሰለ የሰው ልጅ ሁሉ ሲሆን ወንበዴው ደግሞ ዲያብሎስ ነው። የአዳምን ቁስል የፈወሰው ርኅሩኅ ሳምራዊ ራሱ መድኃኔዓለም ሲሆን፣ ይህን ቁስለኛ ወስዶ ያሳደረበት የእንግዶች ማረፊያ ቤት የተባለችው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ናት። በዚህ ዓለም የኖሩና የሚኖሩ የእግዚአብሔር ወዳጆች

ሁሉም እንግዶች ናቸውና፡፡ ነቢዩ ዳዊት «*እስመ ፈላሲ አነ ውስተ ምድር ወነግድ ከመ ኵሉ አበውየ* - እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝና፣ እንደ አባቶቼም እንግዳ ነኝና» እንዳለ፡፡ መዝ.፻፲፰÷፲፱፡፡ የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ያዕቆብን ዕድሜውን በጠየቀው ጊዜ «የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሠላሳ ዓመት ነው» አለው፡፡ ዘፍ. ፵፯÷፱፡፡

ስለዚህ እንግዶች የተባሉት ምእመናነ ክርስቶስ - ክርስቲያኖች በሙሉ ሲሆኑ የእን ግዶች ማደሪያ የተባለችው ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ የማደሪያው ቤት (የቤተ ክርስቲያን) ጠባቂዎች የተባሉት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ናቸው፡፡ *«እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛ ነቢያትን፣ ሦስተኛም አስተማ ሪዎችን … አድርጎአል»* እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ፡፡ ፩ቆሮ.፲፩÷፳፰፡፡ በየዘመኑ ያሉ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የክርስቶስን *መንጋ* (ቤተ ክርስቲያንን) የመጠበቅ አደራ ያለባቸው መሆኑን ሲገልጽም *«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋውና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ»* ይላል፡፡ የሐዋ. ፳÷፳፰፡፡

ራሱን በርኅሩኅ ሳምራዊ የመሰለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእንግዳዎች ቤት ማደሪያ (ለቤተ ክርስቲያን *መምህራን*) የሰጠው ሁለት ዲናሮች ለቤተ ክርስቲያን የተሰጧትን ዋና መጻሕፍት ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ሁለቱን ዲናር ከሰጠው በኋላ በነዚያ ብቻ ሳይወሰን *«ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃ ለሁ»* አለው፡፡ ሉቃ.፲÷፳፱-፴፭፡፡ ይህም የሚያመለክተው በሁለቱ ዲናሮች ማለትም በብ ሉይና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተመሥርተው የረቀቀውን አጉልተው፣ የተሰወረውን ምስ ጢር ገልጠው ምእመናንን የሚያስረዱ የተለያዩ የትርጓሜ፣ የምክር፣ የተግሣጽ፣ የታ ሪክ እና የመሳሰሉትን ድርሰቶች በመድረስ እንዲያስተምሩና የዚህም ተጨማሪ መጻ ሕፍት፣ የመጻፉቸው፣ የድካም ዋጋ እንደማይጠፋባቸው ሲገልጽ ነው፡፡ «እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ» ማለቱ በዳግም ምጽአቱ ዕሴታቸውን እንደሚሰጣቸው ሲናገር ነው፡፡

## የአዋልድ መጻሕፍት ቁጥር ይታወቃልን?

አዋልድ መጻሕፍት የተለያዩና ብዙ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በየጊዜው እየተጻፉና እየተጨመሩ የሚሄዱ ስለሆነ ቁጥራቸው ይህን ያህል ተብሎ ሊወሰን አይችልም፡፡ የአን ድን ነገር ቁጥር ለማወቅ ማቆምን ይጠይቃልና፡፡ በተለይም ደግሞ አዋልድ መጻሕፍት እንደ ቀኖናውያን መጻሕፍት እገሌ መጽሐፍ አንድ፣ እገሌ መጽሐፍ ሁለት ተብለው

ተለይተውና ተወስነው ሊቆጠሩ ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ጸሐፍያን የተጻፉ ስለሆነ ነው። የሚያገኛቸውም ሰው ዐይቶና ተመ ልክቶ ከመሠረታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮና የቤተ ክርስቲያን ትውፊት የሚስ ማሙ ከሆኑ ይጠቀምባቸዋል እንጂ እያንዳንዱ መጽሐፍ በተጻፈ ቁጥር እየታየ በቀኖና ተወስኖ የሚዘለቅ አይደለም፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን አዋልድ መጻሕፍት ቁጥራቸው እጅግ ብዙ መሆኑን ሲገልጽ «አዋልድ እለ አልቦን ኁልቍ፦ ቁጥር የሌላቸው (ብዙ የሆኑ) ልጆች» ብሏል፡፡ መኃ. ፮፥፰፡፡

መሠረታዊው መርህና መመዘኛ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን ትምህ ርት እስከተቀመጠ ድረስ በነዚህ መመዘኛዎች መመዘን የእያንዳንዱ ድርሻ ነው፡፡ ሆኖም ግን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለመንፈሳዊ አገልግሎቷ የምትጠ ቀምባቸውን መጻሕፍት በቅዱስ ሲኖዶስ መዝናና ለይታ መወሰን ትችላለች፡፡ በተለይም በቤተ ክርስቲያን የዕለት ተዕለት አገልግሎት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትንና በስሟ የሚጠሩትን ወይንም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት እንደሆኑ የሚነገሩ ካሉ እነዚህን መርምራ የቤተ ክርስቲያን ከሆኑ ማጽደቅ ካልሆኑ ደግሞ ስህተታቸውን መግለጥና መለየት አስፈላጊ ነው፡፡

## የሐዲስ ኪዳን አዋልድ መጻሕፍት

***በዘመነ ሐዋርያውያን አበው***

ሐዋርያውን አበው አሥራው መጻሕፍትን በመናፍቃን እንዳይቀሰጡ ከመጠበቃቸ ውም በላይ እነርሱም በበኩላቸው ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል፡፡ ለምሳሌም፡-

**ቀሌምንጦስ ዘሮም፡-** በልዩ ልዩ ከተሞች ለሚኖሩ ክርስቲያኖች መልእክታትን ጽፏል፡፡

**ሊካርፐስ፡-** ለፊልጵስዩስ ሰዎች፣ ለሰርምኔስ ክርስቲያኖች መልእክታትን ጽፏል፡፡

**አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፡-** ለኤፌሶናውያን፣ ለማግሬስያውያን፣ ለጥራልያንስ፣ ለሮ ማውያን፣ ለፊላዶልፊያውያን፣ ለሰርምኔሳውያን፣ ለሊካርፐስ፣ ለጠርሴሳውያን፣ ለአ ንጾኪያውያን፣ ለፊልጵስዮሳውያን.... መልእታትን ጽፏል፡፡

**ፒያስ፡-** ዛሬ ሙሉው ጽሑፍ ጠፍቶ ከፊሉ ቢገኝም በዘመኑ ለነበሩ ክርስቲያኖች መል እክት ጽፏል፡፡

**ሄርሜን፡-** «ኖላዊ» የተሰኘ መፍሐፍ ጽፏል፡፡

## *የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች (Apologists) ዘመን*

እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ጠበቆች (Apologists) መምለክያነ ጣዖት የነበሩ ባለሥልጣ ናትና ነገሥታት፣ በክርስቲያኖች ላይ የሚያደርሱትን ግፍና መከራ በተለያዩ ጽሑፎች ከመቃወም ጎን ለጎን የክርስትናን ሃይማኖት ትክክለኛነትና እውነተኛነት ለማስተማርና ለመመስከር ለጣዖታዉያንና ለአይሁዶች ብዙ ድርሳናትን ደርሰዋል፡፡ እነዚህም ሃይማኖ ታቸውን በጽሑፍ ያብራሩና በምስጢር /በሥነ አመክንዮ/ የተከራከሩ ናቸው፡፡ ከእነርሱም ሰማዕትነትን የተቀበሉ ብዙ አባቶች አሉ፡፡ በዚህም ዘመን ከተጻፉት ብዙ ድርሳናት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው፡-

**ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ** (Justin Martyr)**:-** በብሉይ ኪዳን ስለ መሢሕ (ክርስቶስ) መምጣት የተነገሩ ትንቢቶች ሁሉም በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የተፈጸሙ መሆናቸ ውንና የኦሪት መግቦት በወንጌል የተተካ መሆኑን የሚገልጽ ከአንድ ትሪፎን ከተባለ አይ ሁዳዊ ጋር የተደረገ የክርክር መጽሐፍ፣ ስለ ትንሣኤ የጻፈው መጽሐፍ፣

**አቴናጎራስ፡-** ክርስትናን ለመንቀፍና በሥነ አመክንዮ ውድቅ ለማድረግ በማሰብ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲያጠና መጻሕፍቱ ለወጡትና በዚያው ክርስትናን ተቀበለÝÝ የአቴና ፈላስፋ የነበረ ሲሆን ክርስቲያኖችን ሲያሰቃዩ ለነበሩት ማርቆስ ኦሬሌዎስና ኮሞዶስ ለተ ባሉት የሮማ ነገሥታት ከ፻፸፯-፻፸፰ ዓ.ም. የክርስቲያኖችን ንጹሕነታቸውን የሚገልጽና ስለ ክርስትና ሃይማኖት ምክንያታዊነትና ትክክለኛነት የሚያብራራ በሳል የሆነ የጥብቅና መጽሐፍ ጽፏል፡፡ እንዲሁም ሥጋ (ሰውነት) በትንሣኤ የሚነሣ ስለመሆኑ (በእንተ ትን ሣኤ ሥጋ) ጽፏል፡፡

**ቅዱስ ቴዎፍሎስ ዘአንጾኪያ፡-** የተለያዩ የጥብቅናና የሐተታ መጻሕፍትን ጽፏል፡፡

**ቅዱስ ሄሬኔዎስ፡-** የልዮኑ ቅዱስ ሄሬኔዎስ ብዙ መጻሕፍትን ጽፏል። ከእነዚህም በሁሉም ኑፋቄዎች ላይ የጻፈው ወጥ መጽሐፍና (Adversus Hæreses) በተለያየ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የተጻፉ ድርሳናት ናቸው፡፡

### *በዘመነ ሊቃውንት*

በዘመነ ሊቃውንት እጅግ ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል፡፡ መጻሕፍት በብዛት እንዲጻፉ የሆነበት ምክንያትም

፩. ምእመናን በመብዛታቸው እነርሱን በሚገባ ለማስተማር

፪. መናፍቃን በመነሣታቸው መልስ ለመስጠት

፫. ቅዱሳት መጻሕፍትንና ክርስትናን ለሚነቅፉ ፈላስፎችና መምለክያነ ጣዖት መልስ ለመስጠት
፬. በዘመኑ ለተነሡ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ሥነ ምግባራዊ... ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት
፭. በዘመነ ሰማዕታት ያለፉ ሰማዕታትን ሕይወት ለመዘከር
፮. በአካል ለመሔድ የማይቻልባቸው ቦታዎች በመልእክት ለማስተማር
፯. ለተፈጠሩ ክርክሮች ውሳኔ ለመስጠት

ዘመነ ሊቃውንት ዐራት ዓይነት አዋልድ መጻሕፍት የተገኙበት ዘመን ነው።

፩. **መልእክታት፡-** የቤተ ክርስቲያን አበው ሊቃውንት ሃይማኖትን የሚያስተምሩ ልዩ ልዩ መልእክታትን ጽፈዋል። ለምሳሌ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊው ከ፶ በላይ መልእክ ታትን ጽፏል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በስደቱ ዘመን ከ፪፻፴ በላይ መልእክታን ጽፏል። እነ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ሌሎችም አባቶች ብዙ መልእክታትን ጽፈዋል።

፪. **ትርጓሜያት፡-** በዘመነ ሊቃውንት የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የቅዱሳት መጻሕ ፍትን (መጽሐፍ ቅዱስን) ትርጓሜና ምስጢር በማተትና በማብራራት፣ መሠረታዊ አሳባቸውንና ይዘታቸውን በመተንተን ብዙ የትርጓሜ ሥራዎችን ሠርተዋል። በዚያ ዘመን የተነሡ መናፍቃን /በተለይም ግኖስቲኮች/ መጻሕፍትን ለራሳቸው እያጣመሙ በመተርጐማቸው አበው ሊቃውንት የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት በሚገባ እየተረ ጐሙ አስቀምጠዋል። ከታላላቆቹ መተርጉማንም ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፣ ቅዱስ አምፊሎቅዮስ፣ አባ ሄሮኒመስ፣ ቅዱስ ቄርሎስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

፫. **ገድላት፡-** በዚያ ዘመን የነበሩ አበውን እና እማትን ገድል፣ አበው ሊቃውንት እየጻፉ አስቀምጠዋል። ለምሳሌ የብዙዎች ሐዋርያት ገድል ከየቦታው ተሰባስቦ የተጻፈው በዚህ ጊዜ ነው። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ የብዙዎቹን ሐዋርያት ገድል ጽፎልናል። አግናጥዮስ የፖሊካርፐስን የሰማዕትነቱን ገድል ሲጽፍ፤ ይህንንም አውሳ ብዮስ መዝግቦታል። የአግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣ የተፍጻሜተ ሰማዕት ጴጥሮስ ገድ ላት በዚህ ዘመን የተጻፉ ናቸው።

ቅዱስ አትናቴዎስ የአባ እንጦንስን ታሪክ ሲጽፍ አባ ሄሮኒመስ፣ የአባ ጳውሊን፣

የቅዱስ ሂላርዮስን፣ የአባ ማልኮስን ገድላት ጽፏል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከርሱ በፊት ስለነበሩና ሰማዕትነትን ስለተቀበሉ ቅዱሳን ለምሳሌ፤ ስለ ሰማዕቱ ባቢላስ፣ ስለ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣ ስለ ቅዱስ መላጥዮስ፣ ስለ ቅዱስ ኤዎስጣቴዎስ ዘአንጾኪያ በዕለተ ዕረፍታቸው (በበዓላቸው ቀን) ተጋድሎአቸውንና ሕይወታቸውን በተመለከተ ያስተማራቸው ትምህርቶች ይገኛሉ። እንዲሁም ስለ ቅዱሳኑ ስለ ሮማኖስና ስለ በረላም ስብከቶችን ሰብኳል።

፬. **ገዳማዊ ጽሑፎች፡-** *የገዳማዊ ኑሮ በየቦታው የተስፋፋው በዘመነ ሊቃውንት በመሆኑ ገዳማዊ ሕይወትን የተመለከቱ መጻሕፍት በዚህ ዘመን ተጽፈዋል። የበረሃ አበው ንግግ ሮች፣ መጽሐፈ ገነት፣ የባስልዮስ ቀኖና፣ የጳኩሚስ ሕግ ወዘተ ተጽፈዋል።*

## የአዋልድ መጻሕፍት ዓይነት

ከላይ የተለያዩ የአዋልድ መጻሕፍት ዓይነቶችን ያየን ቢሆንም ከላይ ያልተገለጹትንም ጨምረን በአጠቃላይ አዋልድ መጻሕፍት ሲባል የሚወክሏቸውን መጻሕፍት እንደሚከተ ለው ጠቅለል አድርገን እናያለን።

፩. **የትርጓሜ መጻሕፍት፡-** እነዚህ ከላይ እንደተገለጹት የቅዱሳት (የቀኖናውያት) መጻሕ ፍትን ውስጠ ምስጢር የሚያስረዱ መጻሕፍት ናቸው። በተለይም የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የትርጓሜ መጻሕፍት እጅግ በጣም የሚደነቁና ጠቃሚ የሆኑ ናቸው። እንዲሁም የቅዱስ አትናቴዎስና የቅዱስ ቄርሎስ፣ የሦስቱ የቀጰዶቅያ አባቶች (ባስልዮስ ዘቂሣርያ፣ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስና ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ) ትርጓሜዎችም ታላላቅ ሥራዎች ናቸው። በየዘመኑ የተነሡ የሌሎች አበው ትርጓሜያትም ያሉ ሲሆን ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚ ገባ ለማወቅና ለመረዳት እነዚህ ድርሳናት ወሳኝ ናቸው።

፪. **በመናፍቃን ላይ የተጻፉ መጻሕፍት፡-** በተለያየ ዘመን የተነሡ መናፍቃን ለሚያነ ሷቸው የተሳሳቱና አወናባጅ አስተሳሰቦችና እምነቶች መልስ ለመስጠት በየዘመኑ የተነሡ አባቶች ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል። ለምሳሌም ቅዱስ አትናቴዎስ በአርዮስ ላይ፣ አባ ጀሮም በሄሊቪዲየስ ላይ (የእመቤታችንን ዘለዓለማዊ ድንግልና በተመለከተ ለጻፈው አስጸያፊ ነገር)፣ ሄሬኔዎስ በዘመኑ በነበሩ በሁሉም መናፍቃን ላይ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በአ ርዮሳውያን ላይ እና መለኮታዊ ጥበቃን በሚጠራጠሩ ሰዎች ላይ፣ ቅዱስ አውግስቲን በፔላጊዮስ ላይ፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በተለያዩ መናፍቃን ላይ፣ ቅዱስ ቄርሎስ በንስጥሮስ

ላይ እና ሌሎችም ናቸው።

**፫. ገድላት፡-** የአንድን ሰማዕት ወይም ጻድቅ ሕይወት፣ ሥራና ተጋድሎ ዘርዘር ባለ ሁኔታ የያዘ መጽሐፍ «ገድል» ይባላል። «ገድል» በክርስትና ሕይወት ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጡና የሚገጥሙ ፈተናች ጋር የሚደረግ መንፈሳዊ ተጋድሎን የሚያመለክት ነው። ሐዋርያው «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከባለ ሥል ጣናት ጋር፣ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር፣ በሰማያዊም ስፍራ ካሉ ከክፉት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» በማለት እንደገለጸው። ኤፌ.፮፥፲፪። ስለዚህ ገድ ላት የክርስቶስ አገልጋዮች ከክፉዎች ሰዎችና ከአጋንንት ጋር ያደረጉትን ተጋድሎ የሚገ ልጹ መጻሕፍት ናቸው። ገድል የዚያን ጻድቅ ወይም ሰማዕት ዜና ሕይወት ከመነሻው እስከ ፍጻሜው፣ ያሳለፈውን ሕይወት፣ የደረሰበትን ፈተናና እንዴት እንደተወጣው፤ በመጨረሻም ይህን ዓለም ድል አድርጎ ወደ ፈጣሪው የመሄዱን ነገር ያስረዳል። ሐዋ ርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያች በላከው መልእክቱ «...*መከራ ተቀብለን፣ ተተንገላትተንም በብዙ ገድል የእግዚአብሔርን ወንጌል እንናገር ዘንድ በአምላካችን ደፈ ርን*» ሲል የክርስቶስን ወንጌል ለማስተማር የደረሰበትን መከራ «ገድል» ብሎታል። ፩ተሰ. ፪፥፪።

እንዲሁም የመከራውን ዓይነት በሁለተኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ በምዕራፍ ዐሥራ አንድ ላይ ዘርዘር አድርጎ ገልጾታል፤ «በድካም አብዝቼ፣ በመገረፍ አብዝቼ፣ በመታሰር አብዝቼ፣ ... » ፪ቆሮ.፲፩፥፳፫-፳፯። በብሉይ ኪዳን ስለነበሩ አባቶች ተጋድሎም በዕብራውያን መልእክቱ ላይ ዘርዝሮ ተናግሮአል። ዕብ. ምዕ.፲፩። ከቀኖናውያት መጻሕ ፍት አንዱ የሆነው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም፤ በብዛት የሚናገረው የቅዱሳት ሐዋር ያትን ገድል ነው። በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ በየዘመኑ የነበሩ የብዙ ቅዱሳንን ሕይ ወትና ተጋድሎ (ገድል) ይዞአል። መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ካለቀና በቀኖና ከተዘጋ በኋላ ከዘመነ ሐዋርያት ቀጥሎ ለተነሡ ቅዱሳን ደግሞ ተጋድሎአቸውን የሚገልጽ «ገድለ እገሌ» እየተባለ በየስማቸው የሚጠራ የብዙ ቅዱሳን ገድል አለ።

**፬. የሥርዓት መጻሕፍት፡-** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሥርዓቶች አሉ። እነዚህን ሥርዓቶች ሥርዓቱ ከሚሠራላቸው ሰዎች (ማኅበረሰብ) ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛ መድ ዘርዘር ያሉ የአሠራር፣ የአኗኗር፣ ... ሥርዓቶችን የሚገልጹ መጻሕፍት ናቸው። ለምሳሌም በማኅበር (በአንድነት) የሚኖሩ ገዳማውያን መነኮሳት የራሳቸው የሆነ ሥርዓተ ገዳም አላቸው። ለዚህም መሠረቱ በዘመነ ሐዋርያት ያላቸውን ሁሉ እየሸጡ፣

በሐዋርያት እግር ስር እየጣሉ ድሀ ሀብታም የሚባል ነገር ሳይኖር በአንድነት ይኖሩ የነበሩት ማኅበረ ሐዋርያት ናቸው፡፡ የሐዋ.፬÷፴፪-፴፯፡፡ ይህንን የሐዋርያትን ማኅበር አኗኗር ከገዳማዊ ሕይወት ልዩ ሁኔታ አንጻር በመቃኘት ሥርዓተ ገዳም ተሠራ፡፡ ለአንድነት ገዳም ሥርዓት መስፋፋት ታላቅ ሥራ የሠራው ቅዱስ ጳኩሚስ /፪፻፺-፫፻፵፮ ዓ.ም./ ነው፡፡ እርሱም ማኅበረ መነኮሳቱ የሚመሩበትን ሥርዓተ ማኅበረ ገዳም የተቀበለው ከመልአክ እጅ በነሐስ ላይ በተጻፈ ሰሌዳ ነው፡፡ ከዚህ በኋላም ሌሎች ተመሳሳይ ሥርዓተ ገዳማት በእነ ቅዱስ ባስልዮስ፣ በአባ ሲኖዳ እና በሌሎችም ተሠርተዋል፡፡ ሌሎች የሥርዓት መጻሕፍትም ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን … አሉ፡፡

**፭. የጸሎት መጻሕፍት፡-** በግልና በማኅበር (የቤተ ክርስቲያን) ጸሎት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ እነዚህም መጽሐፈ ቅዳሴ፣ መጽሐፈ ተክሊል፣ መጽሐፈ ክርስትና፣ ጸሎተ ሙታን፣ እና የተለያዩ መልካ መልኮች ናቸው፡፡

**፮. ተአምራት፡-** እግዚአብሔር በወዳጆቹ በቅዱሳን እያደረ የሠራቸውና የሚሠራቸው ድንቅ ሥራዎች «ተአምራት» ይባላሉ፡፡ ተአምራት የሚባሉበትም ምክንያት ከተለመደው ነገር ወጣ ያሉ፣ ከዚያም አልፎ ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ የሚፈጸሙ ስለሆኑ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱ በቀጥታ ያደረጋቸውና በወዳጆቹ በሰዎች አማካይነት ያደረጋቸው ብዙ ተአምራት ተመዝግበዋል፡፡ ለምሳሌ ያህልም ሙሴ በግብጻውያን ላይ የተለያዩ መቅሠፍቶችን ማምጣቱ /ዘጸ.፯-፲፪/፣ ቀይ ባሕር ተከፍሎ እስራኤላውያን በደረቅ መሻገራቸው /ዘጸ.፲፬÷፳፩-፴፩/፣ ኢያሱ ገባዖን በሚባል ቦታ ፀሐይን ማቆሙ ኢያ.፲÷፲፪-፲፫፣ ታቦት የተሸከሙት ካህናት ሲገቡበት የዮርዳኖስ ወንዝ ከመፍሰስ ለተወ ሰነ ጊዜ ማቆሙ /ኢያ.፫÷፲፬-፲፯/፣ ሦስቱን ወጣቶች እሳቱን ሳያጠፋ በነበልባሉ ውስጥ አያሉ ማዳኑ /ዳን. ፫/፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡ ዮሐ.፪÷፩-፲፩፣ ሞቶ ከተቀበረ ዐራት ቀን የሆነውን አልዓዛርን ከመቃብሩ ጠርቶ ከሞት ማንሣቱ /ዮሐ.፲፩/ እና ሌሎችም ድንቅ ድንቅ ተአምራት በብሉይም በሐዲስም ተመ ዝግበው ይገኛሉ፡፡ ከመጻሕፍት የቀኖና መወሰን በኋላ በተለያዩ ቦታዎችና ዘመናት እግ ዚአብሔር በወዳጆቹ እያደረ የሚሠራቸው ሥራዎች እየተጻፉ ነቢዩ ዳዊት «መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ - እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው» (መዝ. ፷፯÷፴፭) እንዳለ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ የሚገለጥባቸውና ስሙ የሚመሰገንባቸው ናቸው፡፡

## የአዋልድ መጻሕፍት ተጋላጭነት

አዋልድ መጻሕፍት «በዝተው ተባዝተው ዓለምን እየሞሉ» እስካለንበት ዘመን ቀጥለ ዋል። ከ፬፻፶፩ የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል በኋላ በብሔራዊ ደረጃ ያሉ አብያተ ክርስቲ ያናት በተለመደው ሕግ እና ትውፊት መሠረት አዋልድ መጻሕፍትን እየጻፉ እና እየተ ቀበሉ ተጉዘዋል። ይህ ማለት ግን በመጻሕፍቱ ላይ ፈተና አልደረሰም ማለት አይደ ለም። ፈተናዎቹን በጥቂቱ ቀጥለን እናያለን።

፩. ቅሰጣ፦ የቅሰጣ ሥራ የተጀመረው በአሥራው መጻሕፍት ላይ ነው። አሥራው መጻሕፍትን በመተቸት ግኖስቲኩች እና ሐዲሳን ፕላቶናውያን ከ፪ኛው እስከ ፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሠይፋቸውን መዝዘው ነበር። ለዚህም የተጠቀሙበት መንገድ አስመ ስሎ መጻፍ፣ ከመካከላቸው እየነቀሱ መተቸት፣ እርስ በርስ እንደሚጋጩ አድርጐ ማሳየት፣ በፍልስፍና መንገድ ማሄስ ወዘተ. ናቸው። በተለይም በዘመነ ሐዋርያውያን አበው ቤተ ክርስቲያንን ሲያዉኩ የነበሩት ግኖስቲኮች የራሳቸውን የፈጠራ እምነት እየጻፉ በሐዋር ያት ስም እየሰየሙ ያሰራጩ ነበር። በዚህ ዘመን የነበሩ አበው ዋና ትኩረታቸው አሥ ራው መጻሕፍትን መርጠው፣ ለይተው በቀኖና መወሰን ነበር። በዚህም መሠረት የቅዱ ሳን ሐዋርያትን ወንጌላትና መልእክታት ከግኖስቲኮች የፈጠራ ድርሰቶች በመለየት በልዩ ልዩ ጉባኤያት መጻሕፍቱን መርጠው በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ደነገጉዋቸው።

የአዋልድ መጻሕፍት ዋናው ተጋላጭነታቸው የሚመነጨው በቀኖና ያልተወሰኑና ተሰፍረውና ተቆጥረው ያልተቀመጡ ከመሆናቸው ነው። ከዚህም የተነሣ በባለቤትነት ከያዟቸው አብያተ ክርስቲያናት ወይም ግለሰቦች የእምነትና የአመላካከት ተጽእኖ ሥር የመውደቅ ዕድላቸው ሰፊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በምዕራፍና በቁጥር ተሰፍሮና ተቆጥሮ እንዲቀመጥ የተደረገበት አንዱ ምክንያት ለመለወጥና ሥርዋጽ ለማስገባት ይሞክሩ ለነበሩትና ለሚሞክሩት ሁሉ መንገድ እንዳያገኙ ለማድረግ ነው። እንዲያውም ሆኖ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ሲተረጎም፣ እንዲሁም በተለያየ ዘዴ ክፉዎች ሰዎች አልፎ አልፎ አንዳንድ ቀዳዳ ማግኘታቸው አልቀረም። መንገድና አጋጣሚ ካገኙ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚፈልጉ ትን ከማድረግ ወደ ኋላ የማይሉ ከሆነ በአዋልድ መጻሕፍት ላይ ለውጥ ቢያደርጉና ቢቀስጧቸው አያስደንቅም።

ዲዮናስዮስ የተባለው በሦስተኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ገደማ የነበረው የቤተ ክር ስቲያን አባት እርሱ ጽፎ የላካቸውን መልእክታት ከውስጣቸው ቀንሰውና ቆርጠው አውጥተው፣ ሌላ የራሳቸውን የጨመሩባቸው መሆኑን በመግለጽ ምእመናንን እንዲጠነ ቀቁ አስገንዝቦአል። ዲያብሎስ የሚነዳቸው የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች በአዋልድ መጻሕ

ፍት ላይ የራሳቸውን ኑፋቄ ካስገቡ በኂላ ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮኻል እንደሚባ ለው፤ እንደገና መልሰው ቤተ ክርስቲያንን ለማሳጣትና ለመንቀፍ ይህን እንደ አንድ መንገድ ለመጠቀም መሞከራቸው አልቀረም፡፡ ከዚህም ጋር የቀኖናውያት መጻሕፍት እውነተኛ ልጆች ሳይሆኑ በግንዛቤ ጉድለት ምክንያት አዋልድ መስለው እንዳያሳስቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ አካል የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያን ናቸው የሚባሉትንና በውስጧ ያሉትን የተለያዩ መጻሕፍት መርምሮ ትክክለ ኞቹን አዋልድ መጻሕፍት የማጽደቅ፣ በቅሰጣና በልዩ ልዩ ምክንያት ችግር ያለባቸውን የማስተካከል ወይም ስህተታቸውን በመግለጥ ቤተ ክርስቲያን የማትቀበላቸው መሆኑን መወሰንና ለምእመናን ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ረገድ ቅዱስ ሲኖዶስ በጣም ብዙ ሥራ ይጠበቅበታል፡፡ ምእመናንም መሠረታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በመማ ርና የሁሉም መለኪያ (ቀኖና) የሆኑትን አሥራው መጻሕፍትን (መጽሐፍ ቅዱስን) በመ ማር የተለያዩ ድርሳናትን ከመሠረታቸው አንጻር ለመመዘን እንዲችሉ መሆን ይገባቸ ዋል፡፡ በአዋልድ መጻሕፍት ላይ በቅሰጣም ይሁን በሌላ ምክንያት ይህ ስህተት ነው የሚል ነገር ሲነሣ መደናገጥና መናወጥ አይገባም፡፡ የቤተ ክርስቲያን እምነት የተመ ሠረተው በአዋልድ ላይ ሳይሆን በቀኖናውያት መጻሕፍት ላይ ነውና፡፡

**፪. ጥፋት፡-** በዘመነ ሰማዕታት ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲቃጠሉ ተደርገዋል፡፡ ከአብያተ ክርስቲያናት እና ከምእመናን ቤት እየተሰበሰቡ ጋይተዋል፡፡ ይህ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተነሣው ዘመቻ በ፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኃያል ሆኖ በተነሣው የእስ ልምና ንቅናቄ ምክንያት ጋብ ብሎ እስከ ፲፮ኛኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቆየ፡፡ በ፲፮ኛኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቡርዣውን አብዮት ተንተርሶ በተነሳው የፕሮቴስታንት ንቅናቄ ደግሞ እንደ ገና አገረሸበት፡፡ ፕሮቴስታንቶች አይሁድ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በወሰኑት ውሳኔ በመ መራት የመጽሐፍ ቅዱሳቸውን ቀኖና የሐዲሳን አይሁድ ቀኖናን እንዲከተል አደረጉ፡፡ ቀጥለውም እንደ ይሁዳ መልእክት፣ የዕብራውያን መልእክት የመሳሰሉትን አንቀበልም አሉ፡፡ ይህ ጉዳይ ከባድ ተቃውሞ ቢያስነሣም ፊታቸውን ወደ አዋልድ መጻሕፍት በመመለስ ማናቸውንም አዋልድ መጻሕፍት አንቀበልም ብለው መጽሐፍ ቅዱስን መካን ሊያ ደርጉት ቆረጡ፡፡ የሚገርመው ደግሞ ፕሮቴስታንቶች የሌሎችን መጻሕፍት እየነቀፉ ራሳቸው ግን እምነታቸውን የሚገልጹና ሌሎችን የሚያጥላሉባቸውና ስውር ዓላማቸ ውን፤ ለማሳካት ይረዳቸው ዘንድ በሃይማኖት ስም በዘመቱበት ሕዝብ ላይ እርሱነቱንና ያለፈ ማንነቱን እንዲጠላና እርስ በርሱ እንዲለያይ የሚያደርጉ ጥላቻን የሚዘሩባቸው የተለያዩ ጽሑፎችን የሚጽፉ መሆናቸው ነው፡፡

የደጋጎች አባቶችን ሥራዎች ይነቅፋሉ፣ የራሳቸውን ደግሞ ጥሩነታቸውን ይሰብካሉ። ይኼ «ተጨፈኑ ልብለጣችሁ» ዓይነት ነገር ነው።

የፕሮቴስታንትን ሐሳብ ተከትሎ የተነሣው ኽዴይዝምሽ ደግሞ ሰው እንኳንስ ለቅ ዱሳት መጻሕፍት ለእግዚአብሔር ግድየለሽ እንዲሆን «ሃይማኖት በሰው አእምሮ ውስጥ ብቻ ያለ ሐሳብ ነው» እያለ ከማስተማሩም በላይ «እግዚአብሔር አለ፤ ነገር ግን በቅዱ ሳት መጻሕፍት የተገለጠው ዓይነት አይደለም» የሚል ትምህርት ጨመረበት። ይህም በኋላ ዘመን በአውሮ እና በአሜሪካ ለተፈጠረው የቅዱሳት መጻሕፍት ጥላቻ መሠረት ጣለ። ብዙዎችም እየተነሡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጀምረው ቅዱሳት መጻሕፍትን ማብጠልጠል ሞያ አደረጉት።

ቀደም ብለን በዓለም አቀፍ ደረጃ አዋልድ መጻሕፍት ያለፉበትን ሒደት ተመል ከተናል። ለመሆኑ በእኛ ሀገርስ የገጠማቸው ምንድን ነው? አሁንስ ያሉ ተሐድሶዎች የሚያነሷቸው ጥያቄዎች የየትኞቹ ሒደቶች ውጤቶች ናቸው የሚለውን ደግሞ በአጭሩ እንደሚከተለው እናያለን።

## በኢትዮጵያ የገጠማቸው ሁኔታ

አዋልድ መጻሕፍት በኢትዮጵያ መኖር የጀመሩበትን ጊዜ በትክክል ማወቅ ባይቻ ልም ከብሉይ ኪዳን ዘመን እንደሚጀምር ግን መገመት ይቻላል። በየዘመኑ መጻሕፍት እንደመጡት ሁሉ እነ ዜናሁ ለሙሴን የመሰሉ የብሉይ አዋልድ ቀደም ብለው እንደ መጡ መገመት ይቻላል።

በሐዲስ ኪዳን ከዘጠኙ ቅዱሳን መምጣት ጋር ተያይዘው ቢመጡም በጉልህ የተጻፉ በት ዘመን ግን መካከለኛው ዘመን ነው። ተሰዓቱ ቅዱሳን ሥርዓተ ጳኩሚስን የመሰሉና በሀገራቸው በሶርያ የነበሩ የቅዱሳን ታሪኮችንና አኗኗራቸውን የሚያስረዱ መጻሕፍትን ይዘው እንደገቡ የሚያሳዩ ብዙ አሻራዎች አሉ። በመካከለኛው ዘመን በተለይ በመተርጉም ሰላማ ዘመንና ከእርሱ በኋላ ባሉት ግን ብዙ ገድላት ተተርጉመዋል። የቅዱሳንና የገዳማውያን አኗኗርና ትምህርቶችን የሚያስረዱ መጻሕፍትም ተጠናቅረውና ተጠርዘው የተዘጋጁት ብዙዎቹ ተተርጐመዋል። ከዚህ ጊዜ በኋላ ደግሞ የኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ገድላትም በብዛትና በስፋት እየተዘጋጁ በየገዳማቱ የሚገኙ ሆኑ። በአጭሩ የአዋልድ መጻሕፍት የኢትዮጵያ አኗኗራቸውን በዚህ ጥቂምታ ዘግተን ወደ ገጠሟቸው ነገሮች እንለፍ።

የርተጊዞችን መምጣት ተከትለው የገቡት ካቶሊኮች በራሳቸው ከደከሙት በላይ በልጆቻቸው በቅባቶችና በጸጐች ካደረሱብን ጥፋቶች መካከል መጻሕፍት ላይ የደረሰው

የማይዘነጋው በደል ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች መጻሕፍትን በተለይም ወንጌላትን ከራሳቸው አሳብ /ከጸጋና ከቅባት ሦስት ልደት ጋር/ ለማጣጣም ብዙ ጥፋት አድርሰዋል፡፡ የቀነ ሱለት አለ፤ የፋቁት አለ፤ የለወጡት አለ፤ ብቻ ብዙ ብዙ በደሎችን አድርሰዋል፡፡ ለዚህ አንደ

ዐቢይ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው የኋላ ተርጓሞያን ትርጓሜያቸው ላይ «እንዲህ የሚል ንባብም አለ» እያሉ ሌላውን ቅጂ መጥቀሳቸው ነው፡፡

አዋልድ መጻሕፍትም በዚህ መከራ ውስጥ አልፈዋል፡፡ ሥርዋጽ የገባባቸው፤ አንዳን ዶቹ ጥላቻቸውንም ያሸከሚቸው፣ የፋቁአቸው፤ ለነቀፋ የሚያመች ነገር የጨመሩባቸው፤ ከአንዱ ምንጭ ሲገለበጡ በእጅ የሚገለበጡ በመሆናቸው ምክንያት ታሪክ የተጐረደባ ቸውና የመጥፋትና የመቀነስ ሁኔታ የገጠማቸው፣ ለመተካት በተደረገው ጥረትም ደግሞ ምን አልባት ጭማሪ የገጠማቸውም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከዚህም በላይ የግራኝ አሕመድ ወረራን ተከትሎ ብዙዎቹ በቃጠሎ ወድመዋል፡፡ ፈጽመው ከመጥፋታቸው የተነሣ አሁን በስም የማይጠቀሱም ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል፡፡ ይህ ሁሉ በብዙ ችግሮች ማለፋቸውን የሚያሳየን ጉዳይ ነው፡፡

አሁን ደግሞ መልኩን የለወጠ ፈተናም ገጥሚቸዋል፡፡ ጭራሽ አያስፈልጉም ባዮች ተነ ሥተውባቸዋልና፡፡ አንዳንዶቹማ የበለጡ እየመሰላቸው ቤተ ክርስቲያን የማትቀበላቸውን የጥንቆላና የተሳሳቱ መጻሕፍትንም በመጥቀስ ሁሉንም ከእነዚህ ጋር በመፈረጅ «በመስ ኰት የገቡ» በማለት የ«ይውጡ» መፈክራቸውን ይሰነዝሩባቸዋል፡፡

በመሠረቱ የተሳሳቱና የቤተ ክርስቲያን ያልሆኑ መጻሕፍት በየትኛውም ዘመን አሉ፡፡ ይህ ደግሞ በመጻሕፍትም ብቻ አይደለም፡፡ በነቢያት አንጻር ሐሰተኞች ነቢያት ነበሩ፡፡ በሐዋርያትም አንጻር ደቄቀ አስቄዋን የመሰሉ ሐሰተኞች ሐዋርያት ተነሥተው ነበር፡፡ ከዚህም በላይ ሰይጣን በሰማይ ባሉት በብርሃን መላእክት አምሳል የሚመጣው ተመሳ ሳይ ነገር የሌለው ቅዱስ ነገር ስለማያስደስተውና በእነዚህ ሐሰተኞች ምክንያት እውነ ተኞቹን እንድንጠላለት ስለሚሻ ነው፡፡ ሰይጣን በፍጡራን ብቻ ሳይሆን በጌታችንም አን ጻር ሐሰተኞች ክርስቶሶችንም አስነሥቷል፡፡ እስከዚህ ዓመትም ድረስ ሰዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ ሲሉ እንሰማቸዋለን፡፡ ታዲያ በእነዚህ በሐሰተኞቹ ምክንያት እውነተኞቹን እንጥላን?

በአንዱ ሌላውን ልንጠላ አንችልም፡፡ በሐሰተኞች ክርስቶሶች እውነተኛውን ክርስቶስን ወልደ አብ ወልደ ማርያምን አያስፈልገንም እንደማንለው፤ በሐሰተኞች ነቢያትና ሐዋር ያት ምክንያት እውነተኛ ነቢያትና ሐዋርያትን አልነበሩምም ልንል አንችልም፡፡ ሰይጣን የብርሃን መልአክ እየመሰለ ስለሚገለጥ የመላእክት መገለጥ አላስፈላጊ ነው አይባልም፡፡ እንደዚሁም ሁሉ በአዋልድ አንጻር ዲቃሎች መኖራቸው የማይታበል ነው፡፡ በዲቃሎች ምክንያት እውነተኞቹን አዋልድ አብሮ ማውገዝ ግን ባለማወቅ ከሆነ ሊታረም የሚገ

ባው ነው:: በዓላማ ከሆነ ግን ችግር የለውም:: እንኳን አዋልድ ከክርስቶስም ጋር ፉክክር ለመግጠም የሚፈክሩ ሰዎችን እያየን ነውና:: ስለዚህ እያንዳንዱ በራሱ ተመዝኖ እውነ ተኛነቱ ሐሰተኛነቱ ሊመሰክርለት ይገባል እንጂ የጅምላ የውግዘት መሰል ፉከራ ራስን ከማሳት የሚያልፍ አይደለም::

## ምን ያስፈልገናል

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀብተ ብዙ በመሆኗ ብዙ ሥራዎች ይጠብቋታል:: እርሻ ችን እንደመሬታችን መጠን ነውና:: ምንም የሌለው ያለውን ቢሰድብ አይደንቅም፡ ያለው ግን ታግሶ ለሌለው እያካፈለ ከብስጭትና ከንዴት፣ ከስድብና ከቁጣም ሊያስታግሠው ይገ ባል:: በዚህ መሠረት ቢያነስ ሁለት መሠረታዊ ሥራዎች ይጠብቁናል::

፩ኛ. **እውነተኛውን ትምህርት መስጠት፡-** የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርትና ትውፊት ካለማወቅ የተነሣ በድፍረት ለሚናገሩትና ከመናፍቃን የስድብ ዱላ አንዳንዱን እያነሡ በራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ላይ ለሚሠነዝሩት እውነተኛውን ትምህርት መስጠትና ማስገ ንዘብ የመጀማሪያው ሥራ መሆን ይኖርበታል:: የዋሕ ልጆቿም በእምነት ቢቀበሉትም ዕው ቀቱ አላቸው ማለት አይቻልም:: በዕውቀት ያልተደገፈ እምነት ደግሞ እየቆየ መላላቱ አይቀሬ ነው:: ስለዚህ ለአማኞቿ የሚሆንና ችግራቸውን የሚፈታ ለሚጠይቋቸውም መልስ በመስጠት የሚያስጨንቁበት፣ አንዳንዶችንም ከእሳት የሚያድኑበት ትምህርት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ይጠበቃል::

፪ኛ. **መለየትና ማዘጋጀት፡-** ምንም እንኳን ቀደም ብለን እንዳየነው የአዋልድን ቁጥር መወሰን ባይቻልም የመለየትና ለአገልግሎት የማዘጀት ሥራው ግን ለዐራተኛው ሺህ ዓመት ሊገፋ አይገባውም:: የቀደሙት አበው ጽፈውና ተርጉመው አስረክበውናል:: እኛ ደግሞ በመገልበጥ ጊዜ ሥራዋጽ የገባባቸው ካሉ በማጥራት፣ የተጓደሉትን በማሟላት፣ ዲቃሎቹንና እውነተኞቹን አዋልድ በመለየት ለአገልግሎት ማዘጋጀት ያስፈልጋል:: ለጸሎት የሚሆኑትን፣ ለታሪክና ለዕውቀት የሚሆኑትን፣ ለሕግ ለፍልስፍና የሚጠቅሙትን፣ ... በመለየት ለሁሉም ዓይነት አገልግሎት ዝግጁ መሆን በሚችሉበት መንገድ ማስቀመጥ ያስፈልጋል:: ጌታ በተገለጠ /ዳግመኛ በመጣ/ ጊዜ በቀኝ የሚቆም መጽሐፍና ቅርስ የለም:: የሚቆሙት ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ ሰዎች አግኝተዋቸው ይጠቀሙባቸው ዘንድ፣ ለሀገር ዕድገት፣ ለሕዝብ ሥልጣኔ ጭምር መሠረት የሚሰጡትን ተመራማሪዎች እንዲያገኙአቸው፣ ለምክርና ለተግሣጽ የሚጠቅሙትንም መምህራንና ምእመናን እንዲያገኟቸው መሥራት ይጠበቅብናል:: ካለበለዚያ ቆፍሮ በመቅበር መጠየቃችን አይቀርም፣ እንደ ገብርሃካይ::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*